Free digital copy from ServeNow

# ስለ እግዚአብሔር ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች

ላርስ ቢ ደንበርግ

ServeNow

Free digital copy from ServeNow

*ስለ እግዚአብሔር ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች*

*The Basic Things You Need to Know About God (Amharic)*

ላርስ ቢ. ደንበርግ

የአሳታሚው መብት © 2014 ሰርቭ ናው
በፈቃድ የተወሰደ፤ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

ISBN፡ 978-1-958730-29-4

የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች በሙሉ የተወሰዱት ከመጽሐፍ ቅዱስ አዲሱ መደበኛ ትርጉም ከማጣኛ ጽሑፍ ጋር፤ በቢብሊካ የታተመ ©1993፤2003

The Bible in Amharic©United Bible Societies 1962
Holy Bible, New Amharic Standard Version (አዲሱ መደበኛ ትርጉም). Copyright © 2001 by Biblica, Inc.® በፈቃድ የተወሰደ: መብቱ በዓለም ዙሪያ የተጠበቀ ነው።

በሰርቭ ናው (*ServeNow*) የታተመ፣
1817 Austin Bluffs Parkway #110
Colorado Springs, CO. 80918, USA

Free digital copy from ServeNow

# ስለ እግዚአብሔር ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች

**መግቢያ**

የክርስትና እምነት፣ የሁሉም ነገር ፈጣሪ የሆነ አንድ አምላክ ብቻ ነው በሚል እምነት ላይ የተመሠረተ ነው። በሕሊናችን በግብረ ገብነትና በሃይማኖታዊ ተፈጥሮአችን አማካኝነት በፍጥረተ ዓለሙ እራሱን ሲገልጥልን ቆይቶ፣ አሁን ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ገጾችና እንዲሁም በመጨረሻም በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ተገኝቷል፣ ተገልጧልም።

እርሱን እንዴት ልንገልጸው እንችላለን? ለምሳሌ አንድ የእጅ ሰዓት በአጋጣሚ ወደ ወደመኖር ለመምጣት በጣም ውስብስብ ነው። በተመሳሳይ፣ አጽናፈ ዓለሙም በአጋጣሚ ወይም በእድል ወደ ሕልውና ለመምጣት በጣም ውስብስብ ነው። ሰዓት፣ ሠሪ እንደሚያስፈልገው ሁሉ እንዲሁ አጽናፈ ዓለሙም ፈጣሪ ወይም ሠሪ ያስፈልገዋል። ይህ ፈጣሪ የሆነው አምላክ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኘው አምላክ ነው። እርሱ የፍልስፍና ግንባታ ሳይሆን ስብዕና ያለው፣ ሕያውና ሁሌም የሚሠራ አምላክ ነው።

**እግዚአብሔር ማነው?**

እግዚአብሔር ያለ፣ የፈጠረን፣ የወደደን፣ ስለ እኛ የሚያስብልን፣ ሊያኖረን የሚፈልግና ያድነን ዘንድ ያለውን ምርጥና አንድያ ልጁን የላከልን ነው።

ከዘላለም ጀምሮ አንድ አምላክ ብቻ አለ፣ ይኖራልም። አምላክ ፈጽሞ አልተፈጠረም። እርሱ ፍጹም አፍቃሪ፣ ፍጹም ፍትሐዊ፣ ፍጹም ቅዱስ፣ ፍጹም መሐሪና ለእኛም መልካሙ ሁሉ እንዲሆንልን የሚፈልግ አምላክ ነው።

Free digital copy from ServeNow

## እግዚአብሔር የት ነው?

እግዚአብሔርን፣ አጽናፈ ዓለሙ ይይዘው ዘንድ አይችልም። *በውኑ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በምድር ላይ ይኖራልን? እነሆ፥ ሰማይ ከሰማያትም በላይ ያለው ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም ይልቁንስ እኔ የሠራሁት ቤት እንዴት ያንስ!* (1 ነገሥት 8:27)። እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን የሞላ አምላክ ነው። *ሰው በስውር ቢሸሸግ፥ እኔ አላየውምን? ሰማይንና ምድርንስ የምላሁ እኔ አይደለሁምን? ይላል እግዚአብሔር* (ኤርምያስ 23፡24)።

ብዙ ጊዜ እግዚአብሔርን የምናስበው፣ በሰማይ ውስጥ ብቻ ተወስኖ የሚኖር እንጂ በግዑዙ አጽናፈ ዓለም ውስጥ የሚገኝ አይመስለንም። “እግዚአብሔር የት ነው?” ለሚለው ጥያቄ ግን፣ ባለን እውቀት መልስ የሚሰጥ አለመሆኑ ነው።

## እግዚአብሔር በምን መልክ ይገለጻል?

አብዛኞቹ ሠዓሊዎች እግዚአብሔርን እንደ ሰው ወንድ አስመስለው ያቀርቡታል። መጽሐፍ ቅዱስ፣ አምላክን ለመግለጽ “እርሱ” የሚለውን የግል ተውላጠ ስም ቢጠቀምም አምላክ ግን ወንድ ሰውን ይመስላል አይልም። ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔርን ለመግለጽ እንደ “እንደ” (like) ወይም “እንደ” (as) ያሉ ቃላትን እንጠቀማለን። ወንዶችና ሴቶች የሰው ልጆች በእግዚአብሔር አምሳል እንደተፈጠሩ እናያለን። *እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው* (ዘፍጥረት 1፡27)።

እግዚአብሔርን እንደ ትልቅ ዶሮ አድርጎ የሚያስብ ማንም ባይኖርም፣ በክንፍና በላባ የተገለጹ የእግዚአብሔር መግለጫዎች አሉ። በእርግጥም መጽሐፍ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር መንፈስ እንደሆነና አካላዊ ቅርጽ የሌለው መሆኑን ማለትም፣ ከተራ ቁሳዊ ነገር ያልተሠራ መሆኑን ይናገራል።

Free digital copy from ServeNow

እግዚአብሔር በተፈጥሮ መንፈስ ቢሆንም፣ ከሰው ልጆች ጋር መገናኘት እንዲችል ሥጋዊ መልክን ሊይዝ ይችላል። እግዚአብሔር የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆኖ ወደ ምድር እንደ መጣ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። መጽሐፍ ቅዱስ፣ የሚሞቱ አማኞች ወደ ሰማይ ሄደው *እርሱን እንዳለ ያዩታል ይላል* (1ኛ ዮሐንስ 3፡2)። እርሱን ለማግኘት ወደዚያ እስክንሄድ ድረስ፣ እግዚአብሔር በሰማይ ምን እንደሚመስል የምናውቅበት ምንም መንገድ የለም።

## እግዚአብሔር ምን ይመስላል?

### *እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው*

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ ከመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር ጀምሮ እግዚአብሔር ፈጣሪ ሆኖ ይገኛል። ዘፍጥረት 1፡1 *በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ* ይላል። እግዚአብሔር ሲናገር ሁሉም ወደ መኖር መጡ። እግዚአብሔር በቁሳዊም ሆነ በመንፈሳዊ ዓለም ያለውን ሁሉ፣ ከምንም ነገር ወደ መኖር ጠርቷቸዋል። ነቢዩ ኢሳይያስ፡- *ዓይናችሁን ወደ ላይ አንሡታችሁ ተመልከቱ፤ እነዚህን የፈጠረ ማን ነው? ሠራዊታቸውን በቍጥር የሚያወጣ እርሱ ነው፥ ሁሉንም በየስማቸው ይጠራቸዋል፤ በኃይሉ ብዛትና በችሎቱ ብርታት አንድስ እንኳ አይታጣውም* (ኢሳይያስ 40፡26)። በማለት ተናግሯል።

የዮሐንስ ወንጌልም በተመሳሳይ መንገድ እንዲህ በማለት ገልጾታል፡- *ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም* (ዮሐንስ 1፡3)። በቆላስይስ መጽሐፍ ደግሞ እንዲህ እናነባለን፡- *እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤ የሚታዩትና የማይታዩትም፥ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፥ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው፤ ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል፤* (ቆላስይስ 1፡16)።

አምላክ ቀደም ሲል ከተፈጠሩት ነገሮች አዲስ ነገር ለመፍጠር ሲጠቀም፣ ማለትም በመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ

Free digital copy from ServeNow

ውስጥ ወንድና ሴት ሲፈጠሩ እንደተጠቀመው ሁሉ “እንፍጠር” የሚለውን አገላለጽ ይጠቀማል።

ሁሉንም ነገር የፈጠረው እግዚአብሔር ነው። በእግዚአብሔርና በፍጥረት መካከል ልዩነት አለ። እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው፣ እኛ ደግሞ ፍጥረቶች ነን። ስለዚህ፣ እግዚአብሔር በዙሪያችን በተፈጠሩ ነገሮች ውስጥ ሁሉ አለ የሚለውን አስተሳሰብ እንቃወማለን። እንዲሁም እንደ ፍጡራን፣ ሕይወትን በሰጠን በእግዚአብሔር ላይ ሙሉ በሙሉ ጥገኛ መሆናችንን እንገነዘባለን።

እግዚአብሔር ፈጣሪ ሆኖ ሳለ፣ ፍጥረታቱ መልካም መሆኑን ያረጋግጣሉ። በዘፍጥረት 1 ላይ እግዚአብሔር ፍጥረታትን በፈጠረ ጊዜ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፍጥረት እንዲህ ሲል ደጋግሞ ተናግሯል፡- *እግዚአብሔርም መልካም እንደ ሆነ አየ።* ይህ ማለት ግን፣ ፍጥረት በአሁኑ ጊዜ ፍጹም ነው ማለት አይደለም። አሁን የምናየው ዓለም እግዚአብሔር እንዲሆን ያሰበው ዓለም አይደለም፣ ምክንያቱም ኃጢአት ወደ ዓለም ገብቷልና።

በፍጥረት ውስጥ ያለውን መልካምነት ስንረዳ፣ ሁሉንምና እያንዳንዱን እንደ እግዚአብሔር ፍጥረት እናከብራለን ማለት ነው። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር መልካም አድርጎ የፈጠረው መሆኑን ስናምን፣ ለክፋት ተጠያቂው እግዚአብሔር አይደለም ማለታችንም ነው።

እግዚአብሔር እንደ ፈጣሪ፣ ዓለምን የማስቀጠልና የማደስ ቀጣይነት ያለውን ስራውን ያካትታል። በመዝሙር 36፡6 ላይ፣ እግዚአብሔር ሰውንና እንስሳን እንደሚያድን እናነባለን። እንዲሁም በማቴዎስ 6፡ 26-27 ላይ፣ እግዚአብሔር ለፍጥረታቱ የሚያስፈልጋቸውን እንዴት እንደሚያቀርብና በልግስና እንደሚሰጥ ኢየሱስ ተናግሯል። ጳውሎስ ስለ መጪው የፍጥረት መታደስ በሮሜ 8፡21 ላይ ጽፏል።

እኛ የምንሠራው ነገር ሁሉ፣ ከነባር ቁሳቁሶች ጋር የተጣመረ ወይም በቀደሙት አሳቦች ላይ የተገነባ ነው። እግዚአብሔር ነገሮች ወደ መኖር እንዲመጡ የመናገር ችሎታ አለው፤ ጋላክሲዎችንና የሕይወት

Free digital copy from ServeNow

ቅርጾችን ብቻ ሳይሆን፣ በዛሬ ችግሮች ላይም መፍትሔዎች እንዲመጡ ይናገራል። ኃይሉን እንድናውቀውና ደግሞም እንድንተማመንበት የሚፈለገው ለዚህ ነው።

*ጌታችን ታላቅ ነው፥ ኃይሉም ታላቅ ነው፥ ለጥበቡም ቍጥር የለውም* (መዝሙር 147:5)። *ዓይኖቼን ወደ ተራሮች አነሣሁ፤ ረዳቴ ከወዴት ይምጣ? ረዳቴ ሰማይና ምድርን ከሠራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው* (መዝሙር 121፡1፣2)።

## *እግዚአብሔር ልናውቀው የምንችለው አካል ነው።*

በአንድ በኩል፣ የአጽናፈ ዓለሙን ስፋትና ጥልቀት የፈጠረ አምላክ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ልናውቀው የምንችለው አካል ነው። እርሱ ስለ ራሱ ይነግረናል፣ ነገር ግን ከዚያም ያለፈ ነው። እኛ በግላችን እርሱን ማወቅ እንድንችልና ከርሱም ጋር ዝምድና እንድንመሠርት አድርጎናል። ስለ እርሱ ማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ በቅርበት ልናውቀውም እንችላለን።

*እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ጠቢብ በጥበቡ አይመካ፥ ኃያልም በኃይሉ አይመካ፥ ባለ ጠጋም በብልጥግናው አይመካ፤ ነገር ግን የሚመካው፡- ምሕረትንና ፍርድን ጽድቅንም በምድር ላይ የማደርግ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን በማወቁና በማስተዋሉ በዚህ ይመካ፤ ደስ የሚያሰኙኝ እነዚህ ናቸውና፥ ይላል እግዚአብሔር* (ኤርምያስ 9:23-24)።

## *እግዚአብሔር ልንቀርበው የምንችለው አካል ነው።*

እግዚአብሔር እርሱን እንድናነጋግረውና እኛን በሚመለከትም ነገር ላይ እንድናሳትፈው ይጋብዘናል። መጀመሪያ ወደ እርሱ ስንመጣ መልካም ምግባር እንዲኖረን ወይም የተዋጣልን እንድንሆን አይጠበቅብንም፤ ማለትም ጨዋ፣ በሥነ መለኮት ትምህርት ትክክል፣ ወይም ቅዱስ መሆን አያስፈልገንም። ወደ እርሱ ስንሄድ፣ እንደሆንን እንዲያው እኛን መውደድና መቀበል ተፈጥሮው ነው።

Free digital copy from ServeNow

*እግዚአብሔር ለሚጠሩት ሁሉ፥ በእውነት ለሚጠሩት ሁሉ ቅርብ ነው* (መዝሙር 145፡18)።

## *እግዚአብሔር መንፈስ ነው*

እግዚአብሔር፣ ከእኛ ጋር ግንኙነት ይኖረው ዘንድ ሰው የሆነ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር መንፈስም ነው። ይህ ማለት በቁስ አካል ያልተዋቀረና ተፈጥሮአዊ አካል የሌለው ማለት ነው። እግዚአብሔር ቁሳዊ ተፈጥሮን የፈጠረ ነው፤ ነገር ግን እርሱ ከምንም ቁሳዊ ነገር የተዋቀረ አይደለም። ኢየሱስ በዮሐንስ 4፡24 ላይ፣ *እግዚአብሔር መንፈስ እንደሆነ* ተናግሯል። በ1 ጢሞቴዎስ 6፡16 ላይ ደግሞ፣ *እርሱን ያየና ሊያየውም የሚቻል ማንም እንደሌለ* እናነባለን። ምንም እንኳን ራሱን ለሙሴ የገለጠና ያናገረውም ቢሆንም እንኳ፣ ሙሴ ግን እግዚአብሔርን ፈጽሞ ማየት አልቻለም።

እግዚአብሔር ሙሴን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያነጋግረው፣ በሚነድ ቁጥቋጦ ውስጥ ነበር። ከብዙ ዓመታት በኋላም፣ ሙሴ እግዚአብሔርን፣ *እርሱም፦ እባክህ ክብርህን አሳየኝ አለ። እግዚአብሔርም፦ እኔ መልካምነቴን ሁሉ በፊትህ አሳልፋለሁ፤ የእግዚአብሔርንም ስም በፊትህ አውጃለሁ፤ ይቅርም የምለውን ይቅር እላለሁ፥ የምምረውንም እምራለሁ አለ። ደግሞም፦ ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም አለ። እጄንም ፈቀቅ አደርጋለሁ፥ ጀርባዬንም ታያለህ፤ ፊቴ ግን አይታይም* (ዘጸአት 33፡18-20 እና 23)።

እግዚአብሔር፣ *ማንም ሊያየኝ አይችልም* ሲልና በሌላ መልኩ ደግሞ *ጀርባዬን ታያለህ* ሲል፣ ይህ ተቃርኖ ሊመስል ይችላል። ምንም እንኳ እግዚአብሔር መንፈስ ቢሆንምና ማንም ሊያየው ባይችልም፣ አንዳንድ ጊዜ ግን እግዚአብሔር ራሱን በተለያየ አካላዊ መልክ ለሰዎች ይገልጣል።

እነዚህ የእግዚአብሔር ጊዜያዊ መገለጫዎች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ፊትና እጆች በሚናገርበት ጊዜ፣ በሰዎች መንገድ ስለ እግዚአብሔር እውነት በመግለጽ እንድንረዳው እየሞከረ ነው።

Free digital copy from ServeNow

## *እግዚአብሔር በሁሉ ኃያል ነው።*

እግዚአብሔር ወሰን የለውም፣ ስለዚህም ገደብ የለሽ ኃይል አለው። እርሱ ለሰዎች ውስን ኃይል እንዲኖራቸው ይፈቅዳል፣ ነገር ግን ይህ በምንም መልኩ የራሱን ኃይል አይቀንሰውም። ኃይሉም መሞላት ወይም መታደስ የሚያስፈልገው አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን እንዳረፈ ይናገራል። ይህም ለእኛ አርአያ ለመሆንና የእረፍት ፍላጎታችንን ለማሳየት እንጂ እርሱ ስለሚደክመው አይደለም።

እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው። የገባውን ቃል ለመጠበቅ የሚያስችል ኃይል አለው። እግዚአብሔር በፍጥረት ላይ ሥልጣን አለው፤ ለምሳሌ በግብፅ ምድር ከብዙ መቅሰፍቶች ጋር ያደረጋቸው ተአምራቶችና እንዲሁም ኢየሱስ በውሃ ላይ መራመዱ ተጠቃሾች ናቸው።

በተጨማሪም፣ የእግዚአብሔር ኃይል የታሪክን ሂደት በመቆጣጠር ላይ፣ በተለይም በማዳን እቅዱ ውስጥና የሰውን ሕይወት በመለወጥ ረገድ ምስክር ነው። በማቴዎስ 19፡26 ላይ፣ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን ማን ሊድን እንደሚችል ሲጠይቁት፡- *ኢየሱስም እነርሱን ተመልክቶ፦ ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ሁሉ ይቻላል አላቸው* ይላል። እግዚአብሔር ፈቃዱን በማድረግ ሁሉን ቻይ ነው። የወደደውን ነገር ሁሉ ያከናውናል፣ ይህንንም ለማድረግ ችሎታ አለው። ነገር ግን እግዚአብሔር አመክንዮአዊ ተቃራኒ የሆኑትን፣ ወይም ባህሪውን የሚክዱ ነገሮችን አያደርግም። ይልቁንም ዓላማውን ለማሳካት ይሠራል። የእግዚአብሔር ያልተገደበ ኃይል ከታማኝነቱ ጋር በቅርብ የተያያዘ ነው። እኛ የተገናኘነው፣ ለመዳን ቃል ኪዳን ብቻ ከሚሰጠን አምላክ ጋር ሳይሆን፣ ያንን ለማሳካት ችሎታ ካለው አምላክ ጋር ነው። *የሚጠራችሁ የታመነ ነው፥ እርሱም ደግሞ ያደርገዋል* (1 ተሰሎንቄ 5፡24)።

Free digital copy from ServeNow

***እግዚአብሔር በሁሉ ሥፍራ ይገኛል።***

እግዚአብሔርን ድንበር አያውቀውም። ስለዚህ እርሱ በሁሉም ቦታ ይገኛል። ይህ እውነት በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይነገራል። *እኔ ካንተ ጋር ነኝ* የሚለው ቃል በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን 22 ጊዜ ያህል ተደጋግሟል። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ መልእክቱን ወደ ዓለም እንዲያደርሱ ሲልካቸው፣ ተመሳሳይ ማረጋገጫ ሰጥቷቸዋል።

እርሱን የሥፍራ ውስንነት አይገድበውም። ሥፍራን ወደ መኖር አምጥቷልና እርሱ ወደ አንድ የተወሰነ ነጥብ መጥቶ ሊሰፈር አይችልም። ጳውሎስ በሐዋርያት *ሥራ* 17፡24 ላይ፣ *ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም* አለ።

በተመሳሳይ ጊዜ እርሱ የማይገኝበት ቦታ የለም። ዳዊት፣ በመዝሙር 139፡7-12 ላይ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፡- *ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ፥ አንተ በዚያ ነህ፤ ወደ ሲኦልም ብወርድ፥ በዚያ አለህ። እንደ ንስር የንጋትን ክንፍ ብወስድ፥ እስከ ባሕር መጨረሻም ብበርር፥ በዚያ እጅህ ትመራኛለች፥ ቀኝህም ትይዘኛለች። በውኑ ጨለማ ትሸፍነኛለች ብል፥ ሌሊት በዙሪያዬ ብርሃን ትሆናለች፤ ጨለማ በአንተ ዘንድ አይጨልምምና፥ ሌሊትም እንደ ቀን ታበራለችና፤ እንደ ጨለማዋ እንዲሁ ብርሃንዋ ነው።*

በኤርምያስ 23፡23-24 ላይ ደግሞ፡- *እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ - እኔ የቅርብ አምላክ ነኝ እንጂ የሩቅ አምላክ አይደለሁም። ሰው በስውር ቢሸሸግ፥ እኔ አላየውምን? ሰማይንና ምድርንስ የምሞላ እኔ አይደለሁምን? ይላል እግዚአብሔር።*

እግዚአብሔር በተፈጥሮና በታሪክ ውስጥ ያለና የሚሠራ ነው፤ እንዲሁም እርሱ ከተፈጥሮና ከሰውነት የተለየና ገለልተኛ ወይም ጥገኛ ያልሆነ ነው። ልብ ልንለው የሚገባው ነገር፣ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በሁሉ ውስጥ ነው፤ ሁሉም ነገር ደግሞ በእግዚአብሔር

Free digital copy from ServeNow

ውስጥ ነው  የሚለውን አስተሳሰብ ውድቅ እንደሚያደርገው ነው። እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ ቢኖርም በሁሉም ነገር ውስጥ የለም።

### *እግዚአብሔር ሁሉንም ያውቃል።*

እግዚአብሔር ፍጹም እውቀት ስላለው መማር አያስፈልገውም። እግዚአብሔር አልተማረም፣ አይማርምም። እግዚአብሔር ሁሉን ያውቃል እውቀቱም ወሰን የለውም። ከእግዚአብሔር ምንም ነገር መሰወር አይቻልም።

ይህ፣ በሁሉም ሥፍራ መሆን ከመቻሉ ጋር በቅርብ የተቆራኘ ነው። እናም በመዝሙር 139፡1-4 ውስጥ እንዲህ ተገልጿል፡- *አቤቱ፥ መረመርኸኝ፥ አወቅኸኝም። አንተ መቀመጤንና መነሣቴን አወቅህ፤ አሳቤን ሁሉ ከሩቅ አስተዋልህ። ፍለጋዬንና ዕረፍቴን አንተ መረመርህ፤ መንገዶቼን ሁሉ ቀድመህ አወቅህ፥ የዓመፃ ቃል በአንደበቴ እንደሌለ።*

### *እግዚአብሔር በራሱ መኖር የሚችል ነው።*

ሙሴ፣ በሚነደው ቁጥቋጦ ውስጥ ከማን ጋር እየተነጋገረ እንደሆነ ሲጠይቀው፣ እግዚአብሔር *"ያለና የሚኖር እኔ ነኝ"* አለው።

እግዚአብሔር መጀመሪያም መጨረሻም የለውም። እርሱ ብቻውን አለ። በመላው አጽናፈ ዓለም ውስጥ፣ ምንም ነገር ለእርሱ መኖር ምክንያት አይደለም። እግዚአብሔር ብቻውን። እንዲያውም እርሱን ሌላ ነገር ቢፈጥረው ኖሮ፣ ያ ነገር አምላክ በሆነ ነበር። በሕይወታችን ውስጥ የሚያጋጥሙን ነገሮች ሁሉ ከራሱ ውጪ ከሌላ ነገር ስለሚመጡ፣ ይህ ለአእምሮአችን አስቸጋሪ የሆነ ጽንሰ-አሳብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፣ *በመጀመሪያ እግዚአብሔር* ብሎ ይጀምራል። እርሱ አስቀድሞውኑ ነበር።

### *እግዚአብሔር በራሱ በቂ ነው።*

መጽሐፍ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር በራሱ ሕይወት እንዳለው ይናገራል። *አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው፣ እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ*

Free digital copy from ServeNow

*ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና* (ዮሐንስ 5:26)። በአጽናፈ ዓለም ውስጥ ያሉ ሌሎች ሕይወቶች ሁሉ የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው። እርሱ ምንም ፍላጎት የለውም፤ ስለዚህም የሚያሻሽለው ምንም ነገር የለም። ለእግዚአብሔር ሌላ ምንም አያስፈልግም። እርሱ የኛን እርዳታ አይፈልግም፤ ነገር ግን ከጸጋውና ከፍቅሩ የተነሣ እቅዱን በምድር ላይ እንድናራምድና ለሌሎችም በረከት እንድንሆን ፈቅዶልናል። የምንለወጠው እኛ ነን፣ እግዚአብሔር ግን በፍጹም አይለወጥም።

## *እግዚአብሔር አይለወጥም።*

እግዚአብሔር፣ ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በተደጋጋሚ እንደሚለዋወጡ ሰዎች ዓይነት አይደለም፣ እርሱ የማይለወጥ ነው። ሚልክያስ መልሶ፡- *እኔ እግዚአብሔር ነኝና አልለወጥም* (ሚልኪያስ 3፡6)። የዕብራውያን መጽሐፍ፣ ስለማይለወጠው ስለ ኢየሱስ ባሕርይ እንዲህ ሲል ይናገራል። *ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬም ያው ለዘላለምም ያው ነው።* ዛሬ የእግዚአብሔር *"ስሜት"* ምን እንደሚሆን ማሰብ የለብንም። ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት፣ መለወጥ የምንችለው እኛ ብቻ ነን! ከእግዚአብሔር ጋር ደካማ ግንኙነት ካለን፣ የራሳችን ጥፋት ብቻ ነው። አምላክ ከእኛ የሚፈልገውን ለመማር የምንጥር ከሆነና ለፈቃዱ የምንታዘዝ ከሆነ፣ ከእርሱ ጋር ጥሩ ዝምድና እንዳለን እናውቃለን።

## *እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው።*

እግዚአብሔር በዘላለም ውስጥ ይኖራል። እርሱ የነበረና ለዘላለም የሚኖር ነው። ጊዜ የእርሱ ፍጥረት ነው። እግዚአብሔር ምንም ነገር የማይገርመው፣ ፍጻሜን ከመጀመሪያው ላይ ሆኖ ማየት ስለሚችል ነው። እርሱ ዘላለማዊ ባይሆን ኖሮ፣ ኢየሱስን ለሚከተሉ ሰዎች የሰጠው የዘላለም ሕይወት ተስፋ ብዙም ዋጋ አይኖረውም ነበር።

ለፍጥረታቱ ጊዜን ፈጠረ፤ እርሱ ግን ከጊዜ ውጪ የሚኖር ነው። እግዚአብሔር ሕይወት ነው ማለት፣ እርሱ የሕይወት ምንጭ ነው

Free digital copy from ServeNow

ማለት ነው። ሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ሕይወታቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ ሲሆን፣ እርሱ ግን ሕይወቱን ከውጫዊ ምንጭ አላወጣውም።

## ***እግዚአብሔር ሕያው አምላክ ነው።***

እርሱ **ነው** (IS) ስለሆነ በሕይወት ተለይቷል። ከሌሎች አማልክት በተቃራኒ ሁኔታ፣ እርሱ ሕያው ነው። እግዚአብሔር እኔ ነኝ ሲል፣ እርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ነኝ ማለቱ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት የመጀመሪያዎቹ ቃላቶች፣ *በመጀመሪያ እግዚአብሔር...* የሚሉ ናቸው። ሌላ ነገር ከመፈጠሩ በፊት እግዚአብሔር አስቀድሞ ነበረ። በመዝሙረ ዳዊት 90፡2 ላይ፡- *ተራሮች ሳይወለዱ፥ ምድርም ዓለምም ሳይሠሩ፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ አንተ ነህ ይላል።*

## ***እግዚአብሔር የግል ነው።***

እግዚአብሔር አካል ያለው እንጂ አካል የሌለው ኃይል ብቻ አይደለም። እርሱ በራሱ ግንዛቤና ፈቃድ ያለው፣ ከሌሎች ግላዊ ፍጡራን ጋር የመሰማት፣ የመምረጥና ግንኙነት የመፍጠር ችሎታ ያለው አካል ነው። እርሱ ይናገራል፣ እንዲሁም ሊያናግሩትም ይቻላል። እግዚአብሔር ለራሳችን ዓላማ የምንጠቀምበት ቁስ እንዳልሆነ ልብ ልንል ይገባል። እርሱ ታላቁ **እኔ ነኝ** ያለ፣ አንድና አንድ የሆነ እግዚአብሔር ነው።

## ***እግዚአብሔር ማብቂያ የሌለው የዘላለም ነው።***

ጳውሎስ፣ በ1 ጢሞቴዎስ 6፡15-16 ላይ፡- *ያንም መገለጡን በራሱ ጊዜ ብፁዕና ብቻውን የሆነ ገዥ፥ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ፥ ያሳያል። እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፤ አንድ ሰው እንኳ አላየውም፣ ሊያይም አይቻለውም፤ ለእርሱ ክብርና የዘላለም ኃይል ይሁን፤ አሜን ብሏል።*

Free digital copy from ServeNow

## ***እግዚአብሔር አንድና ብቸኛ አምላክ ነው።***

እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለእስራኤል በሰጣቸው አሥርቱ ትእዛዛት መጀመሪያ ላይ፣ *እግዚአብሔርም ይህን ቃል ሁሉ እንዲህ ብሎ ተናገረ፡- ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ። ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ* (ዘጸአት 20፡1-3)። እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ያዳነ አምላክ መሆኑን ገልጿል፣ ስለዚህም ሌላ አምላክ ሊኖራቸው አይገባም። የእስራኤል ሕዝብ፣ ሌሎች አማልክትን በሚያመልኩ የብዙ አገራት ሕዝብ መካከል ይኖሩ ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ ግን እነዚህ አማልክት አምላክ እንዳልሆኑ ይነግረናል። በኤርምያስ 5፡7 ላይ፡- *እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ልጆችሽ ትተውኛል አማልክትም ባልሆኑ ምለዋል፤ ካጠገብኋቸውም በኋላ አመነዘሩ በጋለሞቶቹም ቤት ተሰበሰቡ።* በኤርምያስ 10 ላይ ደግሞ፣ ነቢዩ ሕያውና ንቁ ስለሆነው ስለ እስራኤል አምላክና ስለ ሌሎች ሰዎች ጣዖታት አማልክት ይናገራል። ነቢዩ፡- *አቤቱ፥ እንደ አንተ ያለ የለም፤ አንተ ታላቅ ነህ ስምህም በኃይል ታላቅ ነው። የአሕዛብ ንጉሥ ሆይ፥ በአሕዛብ ጥበበኞች ሁሉ መካከል በመንግሥታቸውም ሁሉ እንደ አንተ ያለ ስለሌለ፥ አንተን መፍራት ይገባልና አንተን የማይፈራ ማን ነው? በአንድ ጊዜ ሰንፈዋል፥ ደንቍረውማል፤ ጣዖታት የሚያስተምሩት የእንጨት ነገር ብቻ ነው። ... እግዚአብሔር ግን እውነተኛ አምላክ ነው፤ እርሱም ሕያው አምላክና የዘላለም ንጉሥ ነው፤ ከቍጣው የተነሣ ምድር ትንቀጠቀጣለች፥ አሕዛብም መዓቱን አይችሉም። እናንተም፡- ሰማይንና ምድርን ያልፈጠሩ እነዚህ አማልክት ከምድር ላይ ከሰማይም በታች ይጠፋሉ ትሉአቸዋላችሁ። ምድርን በኃይሉ የፈጠረ፥ ዓለሙን በጥበቡ የመሠረተ ሰማያትንም በማስተዋሉ የዘረጋ እርሱ ነው* (ኤርምያስ 10፡6-8 እና 10-12)።

Free digital copy from ServeNow

### *እግዚአብሔር አንድም ሦስትም ነው።*

እግዚአብሔር ራሱን የገለጠው በሦስት አካላት ማለትም በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ነው። ሁሉም አምላክ ተብለዋል፣ እንደ አምላክ ሊመለኩ ይገባል፣ ለዘላለም ይኖራሉ፣ እንዲሁም እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርጋቸው የሚችላቸውን ነገሮች በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ውሃ እንደ እርጥበት፣ ፈሳሽና በረዶ ሊኖር እንደሚችል፣ ደግሞም ውሃ እንደሚሆን፣ እግዚአብሔርም በእነዚህ ሦስት አካላት ራሱን ገልጿል። በተመሳሳይ ጊዜ፣ እግዚአብሔር አንድ ነው እናም ሊከፋፈል አይችልም። ከሦስቱ አንዱ በሥራ ላይ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉም ሙሉ በሙሉ ይሳተፋሉ።

በዘዳግም 6፡4 ላይ፡- *እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው* ይላል። እግዚአብሔር አንድ አምላክ ብቻ ሳይሆን አንድም ደግሞም የማይከፋፈል ነው። አይሁዶችም ሆኑ እስላሞች ክርስቲያኖችን ሦስት አማልክቶች አሏቸው በማለት ይሞግታሉ። እግዚአብሔር ሦስት አካላት፣ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ቢሆንም አንድ ነው፤ ሊከፋፈልም አይችልም። ይህም፣ እግዚአብሔር አንድ አምላክ ብቻ በመሆኑ ልዩ መሆኑን ያሳየናል። የሰማይና የምድር ፈጣሪ የሆነ ሌላ አምላክ የለም። ሕያውና የባሕርይ አምላክ የሆነ ሌላ አምላክ የለም። በሰውነት ማለትም አምላክ በሆነ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ራሱን የገለጠ ሌላ የለም። በእርሱም ለሚያምኑ ሁሉ ፍጹም ነጻ የሆነ መዳንንና የዘላለም ሕይወትን በእርሱ ፊት የሚሰጥ ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ የለም። እግዚአብሔር ልዩ ነው። ልዩነቱም ከምንረዳው በላይ ነው!

### *እግዚአብሔር ጻድቅ ነው።*

ጽድቅ ከሌሎች ፍጥረታት ጋር ባለው ግንኙነት ላይ የሚተገበር የእግዚአብሔር ቅድስና ነው። የእግዚአብሔር ጽድቅ በሕግ ይታያል። መዝሙረ ዳዊት 19፡7-9 ላይ እንዲህ ይላል፡- *የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው፤ ነፍስን ይመልሳል፤ የእግዚአብሔር ምስክር የታመነ*

Free digital copy from ServeNow

*ነው፤ ሕፃናትን ጠቢባን ያደርጋል። የእግዚአብሔር ሥርዓት ቅን ነው፥ ልብንም ደስ ያሰኛል፤ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩህ ነው፥ ዓይንንም ያበራል። የእግዚአብሔር ፍርሃት ንጹሕ ነው፣ ለዘላለም ይኖራል፤ የእግዚአብሔር ፍርድ እውነትና ቅንነት በአንድነት ነው።*

እግዚአብሔር የሚያዝዘው ትክክለኛውን ነገር ብቻ ነው፣ ስለዚህም ትእዛዛቱ በሚታዘዘው አማኝ ላይ በጎ ተጽእኖ ይኖራቸዋል። ጽድቁ ደግሞ እግዚአብሔር በሥራው ትክክል መሆኑን ያሳያል።

## *እግዚአብሔር የፍትሕ አምላክ ነው።*

የእግዚአብሔር ፍትሕ፣ የእርሱ የጽድቅ ፈቃዱ በሥራ ላይ ሲውል ማለት ነው። በኦሪት ዘዳግም 32፡4 ላይ፣ *እርሱ አምላክ ነው፤ ሥራውም ፍጹም ነው፤ መንገዱም ሁሉ የቀና ነው፤ የታመነ አምላክ፥ ክፋትም የሌለበት፥ እርሱ እውነተኛና ቅን ነው* ይላል። መንገዱም ሁሉ ቅን ነው። ዮሐንስ በ1 ዮሐንስ 1፡9 ላይ እንዲህ ሲል ጽፏል፡- *በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።* በዙሪያችን ካለው ኢፍትሐዊ በደል የተነሣ፣ አንዳንድ ጊዜ የአግዚአብሔርን ፍትሕ ማየት አንችልም። ነገር ግን እግዚአብሔር ግፍን ሁሉ የሚፈታበት ቀን ስላዘጋጀ ልንጽናና እንችላለን። *ቀን ቀጥሮአልና፥ በዚያም ቀን ባዘጋጀው ሰው እጅ በዓለሙ ላይ በጽድቅ ሊፈርድ አለው፤ ስለዚህም እርሱን ከሙታን በማስነሣቱ ሁሉን አረጋግጦአል* (ሐዋርያት ሥራ 17:31)።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ጻድቅ መሆኑን ያውጃል፣ ነገር ግን ፍትሐዊ መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ የሚገልጸው የእርሱ ባሕርይ ነው። ከአንዳንድ የውጭ መስፈርቶች ጋር አይጣጣምም። ፍትሐዊ መሆን፣ ለሁሉም ሰው የሞራል እኩልነትን ያመጣል። እኩይ ተግባራት ሲኖሩ፣ ፍትሐዊ ቅጣት እንዲኖር ይጠይቃል። እግዚአብሔር ፍፁም ስለሆነና ፈጽሞ ክፋትን ስላላደረገ ምንም ቅጣት አያስፈልገውም፤ ነገር ግን ከፍቅሩ የተነሣ እግዚአብሔር ራሱ በልጁ በኢየሱስ ማንነት ወደ መስቀል በመሄድ ለክፉ ሥራችን ቅጣት

Free digital copy from ServeNow

ከፈለ። ፍትሑ መሟላት ነበረበት፣ ነገር ግን በኢየሱስ ለሚያምኑ ሁሉ ርኅራኄን አደረገ።

### ***እግዚአብሔር ቅዱስ ነው።***

እግዚአብሔርን ከፍጥረታት ሁሉ የሚለየው እውነታ ይህ ነው። ይህም የሚያመለክተው ልዕልናውንና ፍጹም የሆነ የሞራል ንጽሕናውን ነው። በእግዚአብሔር ውስጥ ምንም ዓይነት ኃጢአት ወይም ክፉ አሳብ በፍጹም የለም። ቅድስናው፣ በአጽናፈ ዓለም ሁሉ ንጹሕና ጻድቅ የመሆኑ ፍቺ ወይም ትርጓሜ ነው። እግዚአብሔር በተገለጠበት ሥፍራ ሁሉ፣ ለምሳሌ በሚቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ ለሙሴ ሲገለጥ፣ እግዚአብሔር በዚያ በነበረበት ጊዜ ያ ሥፍራ የተቀደሰ ይሆናል።

እግዚአብሔር ፍጹም ቅዱስ ነው፤ ምንም የሞራል ወይም የባሕርይ ጉድለት የለበትም። እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ፣ ምንም እርሱ እንኳን ኃያል አምላክ ቢሆንም አንዳች ክፋት መሥራት እንደማይችል ይናገራል። እግዚአብሔር የማይለወጥ ነው። በማንኛውም ጊዜ መለያ ባሕርያቱን ወይም ባሕሪውን አይለውጥም። የሰው ልጅ ለሥነ ምግባር የሚሰጠውን ትርጉም የመቀየር ዝንባሌ ቢኖረውም፣ እግዚአብሔር ግን ሥነ ምግባራዊ ባሕርይውን ከጊዜ ጋር አይሻሻልም፤ ነገር ግን የማያቋርጥና የሚቀጥል ነው።

በዘሌዋውያን 11፡44-45 ላይ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- *እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝና፤ ሰውነታችሁን ቀድሱ፥ ቅዱሳንም ሁኑ፥ እኔ ቅዱስ ነኝና፤ በምድርም ላይ በሚሳብ ተንቀሳቃሽ ሁሉ ሰውነታችሁን አታርክሱ። እኔ አምላካችሁ እሆን ዘንድ ከግብፅ ምድር ያወጣኋችሁ እግዚአብሔር ነኝ፤ እንግዲህ እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተ ቅዱሳን ሁኑ።*

ቅዱስ ማለት የተለየና የተቀደሰ ማለት ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔር ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ የተለየ ነው፣ እርሱ ብቻ እግዚአብሔር ነው ማለት ነው። በተጨማሪም ከሰው ርኩሰት፣ ንጽሕናና ኃጢአት ተለይቷል ማለት ነው። ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ራእይ በቤተ

Free digital copy from ServeNow

መቅደሱ ባየ ጊዜ መላእክትን ከበላዩ አየ። *አንዱም ለአንዱ፡- ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች እያለ ይጮኽ ነበር* (ኢሳይያስ 6:3)።

## *እግዚአብሔር ፍቅር ነው።*

ፍቅር የእግዚአብሔር የባሕርይ አካል ነውና ሐዋርያው ዮሐንስ፡- *እግዚአብሔር ፍቅር ነው* ሲል ጽፏል። ይህንን በ1 ዮሐንስ 4፡9-10 ላይ ማንበብ ስንቀጥል እንደምናየው፣ ስሜታዊና አእምሮአዊ የሆነ የሰው ፍቅር ሳይሆን፣ ራስን በመስጠት ተግባራዊ የሆነ ነው። *በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፥ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና። ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተስሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም።* ይህንን ፍቅር ከእግዚአብሔር ስንቀበል፣ ወገኖቻችንን በተመሳሳይ መንገድ መውደድ ይኖርብናል።

ፍቅርን በተግባር ለማየት ከተፈለገ፣ የኢየሱስን ሕይወት ማጥናት ነው። ስለ ሌሎች ኃጢአት በመስቀል ላይ የከፈለው መሥዋዕትነት፣ የመጨረሻው የፍቅር ተግባር ነው። የእግዚአብሔር ፍቅር፣ ስሜታዊ ሳይሆን በተግባር የተገለጠ መውደድ ነው። ፍቅሩ የሚወደውን ነገር ማለትም ልጁን ኢየሱስን ለመከተል ለወደዱት በነጻ ይሰጣል።

የእግዚአብሔር ፍቅር ከእግዚአብሔር ቅድስና ሊለይ አይችልም። ይህንንም የምንረዳው፣ እግዚአብሔር ልጁን (ፍቅሩን በማሳየት) ለኃጢአታችን ማስተሥረያ (ቅድስናውን በማሳየት) በመላክ ነው።

## *እግዚአብሔር ይቅር ባይ ነው።*

እኛ ኃጢአት እንሠራለን። እኛ ከእግዚአብሔር መንገድ ይልቅ ነገሮችን በእኛ መንገድ ማድረግ ይቀናናል፤ እርሱም ይህንን ሁኔታችንን ያያል፣ ያውቃልም። እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን ኃጢአት ዝም

Free digital copy from ServeNow

ብሎ አይመለከትም፤ ነገር ግን በኢየሱስ በኩል የሚመጡ ሰዎችን፣ በኃጢአታቸው ምክንያት ሊፈርድባቸውና ሊኮንናቸው አይፈልግም። እግዚአብሔር፣ ከእርሱ ጋር ወዳጅነት ከጀመርንበት ጊዜ ጀምሮ ይቅር ይለናል። የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ለኃጢአታችን በመስቀል ላይ በመሞት ዕዳችንን ከፈሎልናል። ከሙታንም ተነስቶ ይህንን ይቅርታ ሰጥቷል። *እርሱም፥ ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው፤ ልዩነት የለምና፤... እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተስረያ አድርጎ አቆመው፤ ይህም በፊት የተደረገውን ኃጢአት በእግዚአብሔር ችሎታ ስለ መተው ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው፥* (ሮሜ 3፡22፣25)።

## ***እግዚአብሔር መሐሪ ነው።***

የእግዚአብሔር ምሕረት እርሱን በጣም ርኅሩኅ ያደርገዋል። የእግዚአብሔር ፍትሕ በኢየሱስ የመስቀል ሥራ የረካ በመሆኑ፣ እርሱን ለመከተል ለወደዱ ሁሉ ምሕረትን የማድረግ ፈቃድና ነፃነት አለው። ምሕረቱ የባሕሪው አካል ስለሆነ መቼም አያልቅም። እግዚአብሔርን ለመናቅ ወይም ለመተው እስካልወደድን ድረስ፣ እግዚአብሔር ከእኛ ከሰዎች ጋር በምሕረት ይዛመዳል።

የእግዚአብሔር ምሕረት፣ ለሕዝቡና ለችግረኞች ያለውን ፍቅራዊ ርኅራኄ ያሳያል። በመዝሙር 25፡6 ላይ፡- *አቤቱ፥ ምሕረትህንና ቸርነትህን አስብ፥ ከጥንት ጀምሮ ናቸውና* ይላል። ኢየሱስ የሕዝቡን ፍላጎት ሲመለከት ርኅራኄን አሳይቷል።

## ***እግዚአብሔር ቻይ ነው።***

ሁል ጊዜ ስለ ሁሉም ነገር 100% ትክክል መሆንን ምን ያህል ትፈልጋለህ? ይህንን መሆን የሚችለው እግዚአብሔር ነው። ጥበቡ ገደብ የለሽ ነው። ታሪክንና ከእርሱ ጋር የተያያዙ የወደፊት ክስተቶችን ጨምሮ የአንድን ሁኔታ ሁሉንም አካላት ይረዳል። እርሱ ትክክለኛውን ነገር እንዲያደርግ ማዘመን፣ መምከር ወይም ማሳመን የለብንም።

Free digital copy from ServeNow

እርሱ ችሎታ ስላለውና ዓላማውም ንጹሕ ስለሆነ ያደርጋል። እርሱን ካመንን አይሳስትም፣ አያሳንሰንም፣ ወይም አያታልለንም። በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ ሙሉ በሙሉ ሊታመን ይችላል።

*አንተን ተስፋ የሚያደርጉ አያፍሩም፤ በከንቱ የሚገበዙ ያፍራሉ* (መዝሙር 25፡3)።

### *እግዚአብሔር ታማኝ ነው።*

እግዚአብሔር ሁልጊዜም ስለ ራሱ በግልጽ ሐቀኛ እንደሆነ ይነግረናል። እርሱ ስለ ራሱ ወይም ስለ እኛ የሚናገረው ሁሉ አስተማማኝ መረጃ ነው። እግዚአብሔር በሚናገረው ነገር ፍጹም ትክክለኛና ሐቀኛ ነው፤ ማለትም ከስሜታችን፣ ከአሳባችንና ከአመለካከታችን በላይ እውነተኛ ነው። የሚሰጠን ቃል ሁሉ ሙሉ በሙሉ ሊታመን ይችላል። በቃሉ ልንይዘውና ልንወስደው እንችላለን።

*ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው። የቃልህ ፍቺ ያበራል፥ ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል* (መዝሙር 119:105፣130)።

### *እግዚአብሔር ቸር ነው።*

እግዚአብሔር ለሚወዱት፣ ባይገባቸው እንኳ እጅግ ታላላቅ ስጦታዎችን መስጠት ያስደስተዋል። ጸጋ፣ ያንን ዝንባሌ የምንገልጽበት መንገድ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋው የሚያልፍበት መስመር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐንስ 1፡17 ላይ፡- *እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናልና፣ ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና፤ ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ ይላል።*

የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ የማይገባ ፍቅር አድርገን ገልጸነዋል። ጸጋ የማይገባ ቸርነት ነው። ይህ ማለት፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚይዘው በሚገባን ነገር ላይ ሳይሆን እንደፍላጎታችን ብቻ ነው። በዘጸአት 34፡ 6 ላይ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- *እግዚአብሔርም በፊቱ አልፎ፡-*

Free digital copy from ServeNow

*እግዚአብሔር፥ እግዚአብሔር መሐሪ፥ ምገስ ያለው፥ ታጋሽም፥ ባለ ብዙ ቸርነትና እውነት፥*

እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባለው ግንኙነት ውስጥ፣ መሠረት የሚያደርገው እንደ ሥራችን ሳይሆን እንደ ቸርነቱ ነው፤ ምክንያቱም እርሱ ከእኛ የሚፈልገው ምንም ነገር የለምና። የእግዚአብሔር ጸጋ በዓለም ውስጥ ልዩ ነገር ነው። በሁሉም ሌሎች ሃይማኖቶች ዘንድ፣ ሰዎች አምላካቸውን ወይም አማልክትን ለማርካት የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን አለባቸው። ነገር ግን እኛ ወደ አምላክ ለመድረስ ከመሞከር ይልቅ እግዚአብሔር ወደ እኛ ወረደ።

## ***እግዚአብሔር መልካም ነው።***

የእግዚአብሔር መልካምነት እርሱን ቸር፣ ልባዊ፣ በጎ አድራጊና መልካም ፈቃዱ ለእኛ ለሰው ልጆች እንዲፈስ የሚያደርገው ነው። ለዚህም ነው በረከቱን ለሚከተሉት ሁሉ የሚለግሰው። የእግዚአብሔር ድርጊቶች የእርሱ መልካምነት ምን እንደሆነ የሚገልጹ ሲሆን፣ ይህንንም ኢየሱስ በዙሪያው ካሉ ሰዎች ጋር ባደረገው የግንኙነት መንገድ በቀላሉ ልናየው እንችላለን።

እግዚአብሔር መልካም ነው። ለልጆቹ የሚበጀውን ያስባል። በመዝሙር 145፡9 ላይ ፡- *እግዚአብሔር ለሚታገሡት ቸር ነው። ምሕረቱም በሥራው ሁሉ ላይ ነው* ይላል።

## ***እግዚአብሔር ጥበበኛ ነው።***

ጥበብ ማለት፣ ፍጹም የሆነ ዓላማን መንደፍና እነዚህን ዓላማዎች ፍጹም በሆነ ትክክልኛ መንገድ ማሳካት መቻል ነው። በሌላ አነጋገር፣ እግዚአብሔር ምንም አይሳሳትም። ጳውሎስ በሮሜ 11፡33 ላይ እንደገለጸው፣ *የእግዚአብሔር ባለ ጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው፤ ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው፥ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም* ብሏል።

Free digital copy from ServeNow

### *እግዚአብሔር ቃሉን ይጠብቃል።*

እግዚአብሔር የገባው ቃል ሁሉ ሙሉ በሙሉ ይፈጸማል። ታማኝነቱ ደግሞ ለዚህ እውነት ዋስትና ይሰጣል። እርሱ አይዋሽም። በመጽሐፍ ቅዱስ፣ እርሱ ስለ ራሱ የተናገረው ነገር ሁሉ እውነት ነው። ኢየሱስ እውነት እንደሆነ ተናግሯል። ይህ ለኢየሱስ ተከታዮች እጅግ አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም የዘላለም ሕይወት ተስፋችን በእርሱ እውነተኛነት ላይ ያረፈ ነው። ኃጢአታችን እንደሚሰረይና ከእርሱ ጋር ለዘላለም እንደምንኖር የገባውን ቃል ያከብራል። የገባውን ቃል ሁሉ ይጠብቃል። በመዝሙረ ዳዊት 57 ፡10 ላይ፡- *ምሕረትህ እስከ ሰማይ ድረስ ከፍ ብላለችና፥ እውነትህም እስከ ደመናት ድረስ ይላል።*

### *እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው።*

ይህ ፍጥረቱን ሁሉ የሚገዛበት መንገድ ነው። ሁሉን አዋቂና ሁሉን ቻይ መሆኑንም የሚያሳይበት መንገድ ነው። ሉዓላዊነቱ፣ እርሱ እጅግ መልካም እንደሆነ የሚያውቀውን ነገር ለማድረግ ሙሉ በሙሉ ነጻ ያደርገዋል። የሚሆነውን ሁሉ በሉዓላዊነት የሚቆጣጠር አምላክ ነው። አሁንም ነጻ ምርጫ አለን፤ ስለሆነም ለሕይወታችን ምርጫ ኃላፊነት አለብን።

### *እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ያደርጋል።*

በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ያለው ቃል ኪዳን፣ ከምልክት ወይም ከቃል ኪዳን ጋር የሆነ መለኮታዊ ሕገ መንግሥት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ኪዳኖች መካከል ጥቂቶቹ እነሆ፡-

- በዘፍጥረት 9 ላይ እግዚአብሔር ከኖኅና ከዘሮቹ ጋር የገባው ቃል ኪዳን፣ እግዚአብሔር ያለ አንዳች መጠራጠር ምድርን ዳግመኛ በጎርፍ እንደማያጠፋ ቃል የገባበት ነው። የዚህም ቃል ኪዳን ምልክት ቀስተ ደመና ነው።

Free digital copy from ServeNow

- በዘፍጥረት 15 እና 17 ላይ እግዚአብሔር ከአብርሃምና ከዘሩ ጋር የገባው ቃል ኪዳን ነው። ይህም ቃል ኪዳን በእግዚአብሔር ምርጫና ጸጋ ላይ የተገነባ ነው። በዘፍጥረት 15፡6 ላይ፡- *አብራምም በእግዚአብሔር አመነ፥ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት* ይላል። የዚህም ቃል ኪዳን ምልክቱ መገረዝ ነው።
- በዘጸአት 19-24 ላይ፣ በኮሬብ ተራራ (ሲና ተብሎም ይጠራል) እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የገባው ቃል ኪዳን ነው። እዚህ ላይ፣ ቃል ኪዳኑና ሕጉ የተያያዙና የተሳሰሩ ናቸው። እግዚአብሔር በዘጸአት 19፡5 ላይ፡- *አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ ኪዳኔንም ብትጠብቁ፥ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆኑልኛላችሁ፤* ይላል። የዚህ ቃል ኪዳን ምልክት የቃል ኪዳኑ ታቦት ነው።
- ትንቢታዊው ቃል ኪዳን፣ አዲስ ሕገ መንግሥት ለመመሥረት በተከታታይ ነቢያት በኩል የተሰጠ መለኮታዊ ቃል ኪዳን ነው። ለምሳሌ ኤርምያስ 31፡31-34ን ተመልከት። ይህም እግዚአብሔር *ሕጉን በልቡናቸው የሚያኖርበት የጸጋ ቃል ኪዳን ነው* (ኤርምያስ 31፡33)።
- አዲሱ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህ አዲስ ቃል ኪዳን ከኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራ መምጣት ጋር የተያያዘ ነው። ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በመጨረሻው ራት ላይ የጌታን እራት ወይም ቅዱስ ቁርባን ባቋቋመ ጊዜ፣ *እንዲሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን አንሥቶ እንዲህ አለ፡- ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው* (ሉቃስ 22፡20)። በዕብራውያን ምዕራፍ 8 ላይ፣ በኢየሱስ እንደ ሊቀ ካህን ሆኖ ስለሚመጣው አዲስ ቃል ኪዳንና እግዚአብሔር በነቢያት የሰጠውን ተስፋ እንደፈጸመ እናነባለን። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች እንዲህ ብሎ በመጻፍ ስለዚህ ቃል ኪዳን ተናግሯል፡- *እናንተም በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በቀለም አይደለም፥ ሥጋ በሆነ በልብ ጽላት እንጂ በድንጋይ*

Free digital copy from ServeNow

*ጽላት ያልተጻፈ፥ በእኛም የተገለገለ የክርስቶስ መልእክት እንደ ሆናችሁ የተገለጠ ነው። በክርስቶስም በኩል ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ያለ እምነት አለን። ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው እንጂ፥ በገዛ እጃችን እንደሚሆን አንዳችን እንኳ ልናስብ ራሳችን የበቃን አይደለንም፤ እርሱም ደግሞ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን፤ ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል* (2 ቆሮንቶስ 3፡3-6)።

የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ከዘላለም ጀምሮ ወደ ዓለም የመጣው፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት፣ ሞትና ትንሣኤ ነው። ይህ የድነት ሥራ በጊዜ ፍጻሜ ላይ ከክፉ ሁሉ መቤዠትን የሚያመለክት ስለሆነ ገና ሙሉ በሙሉ አልተጠናቀቀም።

### *አምላክ እንድናመልከው ይፈልጋል።*

ኢየሱስ በዮሐንስ 4፡23 ላይ ሲናገር፣ *ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና"* ብሎ ነበር።

እግዚአብሔርን በእውነት የሚያመልኩ፣ አምልኮውን በመንፈስና በእውነት በሚያደርጉበት ጊዜ ላይ እንገኛለን። እግዚአብሔር፣ ሰዎች እርሱ በፈቀደው መንገድ እንዲያከብሩትና እንዲያመልኩት ሁልጊዜ ይፈልጋል። ይህንን ያደረጉ ሰዎች ሁል ጊዜ ተቀባይነት ያላቸው ሲሆን፣ ይህንን ማድረግ ያልቻሉት ግን ሁልጊዜም ውድቅ ይደረጋሉ። ይህ አይቀየርም።

### *እግዚአብሔር መዳናችንን ያረጋግጣል።*

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ዓለምን እንደፈጠረና፣ ታሪክን ከዘላለም በተዘጋጀ እቅድ ውስጥ እንዲገለጥ ሲመራ እናያለን። ይህ እቅድ፣ ከሕዝቦቹ ጋር ኅብረትን የመፍጠር ፍላጎቱን ይገልጻል።

ጳውሎስ በኤፌሶን 3፡8-12 እንዲህ ይላል፡- *…ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ባለ ጠግነት ለአሕዛብ እሰብክ ዘንድ፥ ሁሉንም በፈጠረው*

Free digital copy from ServeNow

*በእግዚአብሔር ከዘላለም የተሰወረው የምሥጢር ሥርዓት ምን እንደሆነ ለሁሉ እገልጥ ዘንድ ይህ ጸጋ ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ለማንስ ለኔ ተሰጠ፤*

*ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አሁን በቤተ ክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ስፍራ ውስጥ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት ትታወቅ ዘንድ፤ ይህም በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የፈጸመው የዘላለም አሳብ ነበረ፥ በእርሱም ዘንድ ባለ እምነታችን በኩል በመታመን ድፍረትና መግባት በእርሱ አለን።*

## እግዚአብሔር ከእኔ የሚፈልገው ምንድን ነው?

አምላክ አጽናፈ ዓለሙን ሁሉ ለእኛ ለሰዎች እንድንኖርበት ከፈጠረው፣ አንዳች እቅድ በአእምሮው ይዞ መሆን አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በተቻለ መጠን ብዙ ሰዎች እርሱን እንዲወዱትና ከእርሱ ጋር ዘላለማዊነትን እንዲመርጡ ይፈልጋል ይላል። የእግዚአብሔር የምግባር መለኪያ በአስተሳሰብና በድርጊት ፍጹም ስለሆነ፣ የእግዚአብሔርን መስፈርት በራሳችን ማሟላት በጣም አስቸጋሪ ይሆንብናል። እግዚአብሔር ግን እኛን በጣም ስለወደደን በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን የሰውን መልክ ለብሶ በምድር ላይ ኖረ። ስሙም ኢየሱስ ነበር።

*በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን። እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም፥ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፥ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፥ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ* (ፊልጵስዩስ 2፡5-8)።

ዋና ዓላማው ፍጹም ኃጢአት የሌለበትን ሕይወት በመምራት፣ ለኃጢአታችን የመጨረሻውን መሥዋዕትነት ማቅረብ ነበር። ለምናደርገው መልካም ያልሆኑ ነገሮች ብቻ ሳይሆን፣ በተፈጥሮ ለሆንነው ክፉ ማንነትም ከፍሏል። *ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ*

Free digital copy from ServeNow

*እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም* (ዕብራውያን 4፡15)።

እርሱ በመስቀል ላይ ሞተ። *እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር፥ በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና* (ቆላስይስ 1፡19-20)።

እርሱ ከሞት ተነሣ። *ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ወደ ፊት እንዳይሞት ሞትም ወደ ፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና። መሞትን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ለኃጢአት ሞቶአልና፤ በሕይወት መኖርን ግን ለእግዚአብሔር ይኖራል* (ሮሜ 6፡9-10)። ጻድቅ የተባልነውና ከኃጢአት ነጻ የሆንነው፣ በኢየሱስ በማመንና ለኃጢአት ባቀረበው መሥዋዕት ነው። በኢየሱስ ስታምን እርሱን መከተል ትፈልጋለህ። የክርስቶስን መልክ እንድትመስል በየቀኑ በሚመራህ በመንፈስ ቅዱስ ያስታጥቅሃል። *ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና፤* (ሮሜ 8፡29)። በኢየሱስ የሚያምኑ ጻድቃን ተብለው ተጠርተዋል፤ እናም ከእርሱ ጋር ለዘላለም ይኖራሉ።

Free digital copy from ServeNow

## ከብሉይ ኪዳን የተወሰኑ የእግዚአብሔር ስሞች ፡-

***ኤሎሂም፡-***
"እግዚአብሔር" ማለት ሲሆን፣ የእግዚአብሔርን ኃይልና ኃያልነት የሚያመለክት ነው።

***አዶናይ፡-***
ትርጉሙ "ጌታ" ማለት ሲሆን፣ የእግዚአብሔር ጌትነት ማጣቀሻ ነው።

***ይሖዋ ወይም ያህዌ፡-***
የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ማዳን የሚያመለክት ነው።

***ይሖዋ፡-***
ማካድዴሼም ማለትም "የሚቀድስህ ጌታ" ማለት ነው።

***ይሖዋ ሮሂ፡-***
ማለት፣ "ጌታ እረኛዬ" ማለት ነው።

***ይሖዋ ሻማህ፡-***
ማለት፣ "በአሁኑ ያለው ጌታ" ማለት ነው።

***ይሖዋ ራፋ፡-***
ማለት፣ "መድኃኒታችን (ፈዋሻችን) ጌታ" ማለት ነው።

***ይሖዋ ጽድቀኑ፡-***
ማለት፣ "እግዚአብሔር ጽድቃችን" ማለት ነው።

***ይሖዋ ይርህ፡-***
ማለት፣ "ጌታ ይሰጣል" ማለት ነው።

***ይሖዋ ኒሲ፡-***
ማለት፣ "ባንዲራችን ጌታ" ማለት ነው።

***ይሖዋ ሻሎም፡-***
ማለት፣ "እግዚአብሔር ሰላም ነው" ማለት ነው።

***ይሖዋ ሰንበት፡-***
ማለት፣ "የሠራዊት ጌታ" ማለት ነው።

***ኤልሻዳይ፡-***
ማለት፣ "ሁሉን ቻይ አምላክ" ማለት ነው።

Free digital copy from ServeNow

## ሌሎች የእግዚአብሔር ስሞች

ሁሉን ቻይ

ሊቀ ካህናት

ሕያው ምንጭ

ሕያው ድንጋይ

መልካም እረኛ

መመሪያ

መምህር

መሠረት

መሢሕ

መስፍን

መንገድ

መካር

መደበቂያ ቦታ

ሙሽራ

ሰሪ

ሸክላ ሠሪ

ቅርንጫፍ

ቅድስት

ቃል

በር

ቤዛ

ብሩህ

ታማኝና እውነተኛ

ታላቁ ሐኪም

ነብይ

ናዝራዊ

አልፋ

አማላጅ

አማኑኤል

አሜን

አስታራቂ

አባ

አንድ

አዳኝ

አገልጋይ

ኢየሱስ

እኔ ነኝ

እውነት

ኦሜጋ

ክርስቶስ

ዓለት

የሕማም ሰው

Free digital copy from ServeNow

የሕይወት እንጀራ

የመጨረሻ አዳም

የማለዳ ኮከብ

የማዕዘን ድንጋይ

የሰላም ካህን

የሰው ልጅ

የሳሮን  ጽጌረዳ

የቤተ ክርስቲያን ራስ

የተቀባ

የእረኛ አለቃ

የነገሥታት ንጉሥ

የእግዚአብሔር ልጅ

የእግዚአብሔር መንፈስ

የእግዚአብሔር ቃል

የእግዚአብሔር በግ

የክብር ንጉሥ

የዓለም ብርሃን

የዘላለም አባት

የዳዊት ልጅ

የዳዊት ሥር

የፈጣሪ ፍቅር

የጥንት

ድንቅ

ጋሻ

ጌታ

ግርማ ሞገስ

ጓደኛ

ጠበቃ

ጥላ

ጽድቅ

ፍቅራዊ ደግነት

Free digital copy from ServeNow

## ለውይይት እና ምክክር የቀረቡ ጥያቄዎች

- እግዚአብሔርን እንዴት መግለጽ ወይም ማስረዳት እንችላለን?

- እርሱ ማን ነው?

- ዛሬ የት ነው ያለው?

- እግዚአብሔር ምን ይመስላል? የእርሱ ባህሪያት ምንድን ናቸው?

- አንተ/ቺ እና እኔ በግል እናውቀዋለን?

- እግዚአብሔር ሦስት ነው ማለት ምን ማለት ነው?

Free digital copy from ServeNow

- እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ያደርጋል ማለት ምን ማለት ነው?

- እግዚአብሔር ከእኔ የሚፈልገው ምንድን ነው?

- እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ስሞች ተገልጧል። አንዳቸውን ታስታውሳለህ?

Free digital copy from ServeNow